ሰሚ ያጣው ዶሴ

የምስራቅ ጎጃም ዞን ዉሃ መስኖና ኢነርጂ ልማት መምሪያ ሠራተኞች በመደመር ስሌት ላይ ሁነው የመምሪያውን የዘቀጠ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ማድረሳቸውን ከደረሳቸው አካላት መረጃዉን አግኝቼ የመፍትሔ ጥያቄ ያቀረቡት ጊዜ ብዙ ወራት ቢሞላዉም እስካሁን ምንም መፍትሔ እንዳልሰጧቸዉ ለማረጋገጥም ሞክሪያለሁ ስለሆነም ሰሚ ያጣው ዶሴ ብየ ሰይሜዋለሁ። ምክንቱም ሚስጢር ስለሆነብኝ ????

ጉዳዩን በፊርማቸው አረጋግጠው ያቀረቧቸውን የዘቀጠ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን እንደሚከተለው አጠናቅሬዋለሁ

ለምስ/ጎ/ዞን/አስተዳድር

ለምስ/ጎ/ዞን/ገጠር ፖለቲካ ዘርፍ

ለምስ/ጎ/ዞን/ከተማ ፖለቲካ ዘርፍ

ለምስ/ጎ/ዞን/ብአዴን ጽ/ቤት

ለምስ/ጎ/ዞን/ፍትህ መምሪያ

ደ/ማርቆስ

ጉዳዩ፡- የመ/ቤታችንን ችግር ስለማሳወቅና መፍትሄ ስለመጠየቅ

የምስራቅ ጎጃም ዞን ውሃ መስኖና ኢነርጂ ልማት መምሪያ ለማህበረሰቡ/ለህዝብ/ ተገቢዉን አገልግሎት እንዲሰጥ በአዋጅ የተቋቋመ መሆኑ ይታወቃል።

ነገር ግን መስሪያ ቤቱ ከፍተኛ የሆነ የመልካመ አስተዳድር ችግር ያለበት በመሆኑና የተቋሙ ህልዉና አስከፊ ደረጃ ላይ የደረሰ ስለሆነ ችግሮቹን በመለየት በፊርማችንም በማረጋገጥ ከዚህ በታች በዝርዝር እያሳወቅን በእናንተ በኩል አስፈላጊውን የማጣራት ስራ ተሰርቶ ተገቢ መፍትሄ እንዲሰጠን እንጠይቃለን።

በዚህም መሰረት፡-

በጀት አጠቃቀምን በተመለከተ፡-

በህገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የበጀት እጥረት መኖሩ እየታወቀ ለተፈለገለት ዓላማ ሳይዉል ከፍተኛ ለሆነ ለህብት ብክነት ተጋልጧል።ይህም የሆነዉ ፡-

ሀ. የቢሮ ግንባታ ይሠራል በሚል እንጨት፣ ቆርቆሮ፣ ድንጋይ፣ቺፑድና ሚስማር ከ 3 ዓመት በፊት ተገዝቶ የግንባታ ቁሳቁሱ እየባከነ ያለ ሲሆን ቆርቆሮዉ ግን የት እንደደረሰም አይታወቅም

ለ. ተገቢ ያልሆነ አበል በመክፈል፡- ቢሮ ላይ ቁጭ ብለዉ በመስክ ፀሐይና ብርድ እየተፈራረቀባቸዉ ላባቸዉን እንደዉሃ ከሚጠቀሙት ባለሙያዎች የበለጠ በቅርበትና ጓደኝነት አበል መክፈል እንዲሁም ፍህታዊ ያልሆነ የአበል ቀን ጭማሪ መስጠት በተጨማሪም በድግግሞሽ ማዉጣትና እንዲያወጡ መፍቀድ ቀዳሚ ተግባር ተደርጎ የመ/ቤቱ በጀት ለግለሰቦች ማዋል

ሐ. በየዓመቱ ለቢሮ ቁሳቁስ (ኮምፒዉተር፣ ወንበርና ጠረጴዛ) መግዣ የሚበጀትን በጀት በወቅቱ ግዥ ባለመጠየቅ ምክንያት ተሰብሳቢ እየተደረገ በተቋሙ ቁሳቁስ (ኮምፒዉተር) እጥረት ምክንያት የተፈለገዉ ስራ እየተሰራ እንዳልሆነ እንዲወሰድልን።

መ. በክልሉ በኩል የሚመደቡ የፕሮግራሞች በጀት ፕሮግራሙ በሚፈልገዉ ዓላማ ላይ አለማዋል።

ሠ. የመስሪያ ቤት መኪኖችን ለግንባታ ክትትል፣ ለዲዛይን ሥራ፣ ወረዳዎችን ተዟዙሮ ለመደገፍና በመስክ ስራዎችን ለመቃኘት ሳይሆን ሠራተኛዉን በትራንስፖርት እየላኩ የቢሮ መኪናዉን ለግለሰብ አገልግሎት ከመስጠታቸዉ በተጨማሪ የነዳጂ ወጪ ከመ/ቤቱ እንዲወራረድ በማድረግ በጀቱ አላገባብ እየባከነ ስለሆነ መፍትሔ ያስፈልጋል።

ሥራን በወቅቱ አለመገምገምና በተገቢዉ ሁኔታ አለመምራት

ሀ. የማኔጂመንትን አባላትን በእኩል አይን አይቶ ያለመሰብሰብና ስራን አለመገምገምና አለማወያየት ፡- ሁሉንም ሂደቶች አሳታፊ በሆነ መልኩ ሥራን ገምግሞ ከመስራት ይልቅ ማኔጂመንቱን በመከፋፈልና ፍፁም አምባገነን በሆነ መልኩ ከ 15 ዓመት በላይ የመራሁት መምሪያ ስለሆነ ሁሉን እኔ አዉቀዋለሁ በማለት ሌላዉን ቡድን መሪና ሠራተኛ ዝቅ ማድረግና ማንቋሸሽ በመምሪያችን የተለመዱና የዕለት ተለት ተግባራት ከሆኑ ቆይተዋል

ለ. የሰዉ ኃይል ምደባ ፍላጎት ጥያቄ በተመለከተ፡- በመምሪያዉ የሰዉ ኃይል ማሟላት ስምሪት ለመምሪያዉ ቅድሚያ ለሚሰጠዉ መደብ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንዲሟላና አሳታፊነትን ያረጋገጠ እንዲሆን ከማድረግ ይልቅ በማን አለብኝ መንፈስ በህግ የተሰጠኝ መብት ነዉ በማለትና እራሱን ከተጠያቂነት ለማዳን ዉክልና በመስጠት ቅድሚያ መሰጠት ለሌለበት መደብና የወረዳዎቹን ባለሙያዎች ተሳታፊ በማያደርግ መልኩ የሚፈልገዉ ሰዉ እንዲመደብ ተደርጎ የዉጭ ዝዉዉር እንዲፈፀም የተደረገበትና በተግባር ማጭበርበሩ ተረጋግጦ በትግል የቀረበት ሁኔታ መፈጠሩ

ሐ. ለባለሙያው በወቅቱ ሥምሪት አለመስጠት፡- የሂደት አሰተባባሪዎችን ሳያሳትፍ እንደፈለገ የሚፈልገዉን በመምረጥ አምባገነናዊ በሆነ አካሄድ እራሱ በማሰማራት አሱ እንዲመለከና እንዲሞገስ ከመፈለግ በተጨማሪ የስራዉ ወቅት ካለፈ በኋላ ወከባ በመፍጠር ባለሙያዉን ማሸማቀቅ ዋነኛ ተግባሩ ነዉ

መ. የቢሮ ቁሳቁስ (ኮመፒዉተር) አለማሟላትና ለሂደቶቹ የኮመፒውተር ፍሀታዊ ስርጪት አለመኖር፡- በወቅቱ ግዥ ባለመጠየቅ በመጣ የኮምፒዉተር እጥረት ችግር እንዳለ ሁኖ ያለዉ ኮምፒዉተር ግን ፍፁም ኢፍሀታዊ ስርጪት ከመሆኑ በተጨማሪ በቤታቸዉ አስቀምጠዉ ልጆቻቸዉን እያስተማሩበት አንድም ቀን እንኳ የቢሮ ስራ ሲሰራ ታይቶ የማይታይበት ሁኔታ እያለ ለምን ስራ ይጎዳል? ልምን ይሆን ማስመለስ የተሳነዉና ለሚሰራበት የማይሰጠዉ? መልሱ ግልፅ ነዉ ቡድንተኝነት

ሠ. ዉክልና መስጠትን በተመለከተ፡- የመንግስትና የድርጂት ሥራ ሲኖርም ሆነ ሳይኖር ከዓመቱ ቀናት ከ 90% በላይ በዉክልና መመራቱና የሚወክሉ ሰዎችም መምሪያዉ የሚጠይቀዉን የቴክኒካል ብቃት የሌላቸዉ መሆንና የቡድኑ አጃቢዎች መሆናቸዉ እንዲሁም በቢሮ እያለ አበል ለማወራረድና ለመጠቀም ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ዉክልና ያለማወረድ የተለመደ መሆን

ረ. ቡድንተኝነት በባለሙያው መፍጠር፡- በፖለቲካ አይን የተሾመ የመምሪያ ኃለፊ ከእሱ በማይጠበቅ ሁኔታ የድርጂቱ ጠላት የሆነዉን ቡደንተኝነት በመፍጠር የራሱን ቡድን ብቻ በመደገፍ በሠራተኛዉ ዘንድ እርስ በርስ መጠራጠር፣ አለመተማመንንና ሥራን ተግባብቶ በአንድነት እንዳይሰራና ችግር እንዲፈጠር ተደርጓል። በዚህም ቡድናዊ አመራር ጥላቻ የተነሳ በርካታ የድርጂት አባላት መልቀቂያ ጠይቀዋል፤ ድርጅቱንም እንዲጠላ እያደረገዉ ስለሆነ መፍትሄ ይሻል

ሰ. መሬት ላይ የሌለን ተቋም ሪፖርት ማድረግ፡- ሥራን በጋራ ገምግሞ ካለመምራት የተነሳ በዓመቱ ተገባ ተብሎ ለአስተዳድር ምክርቤትና ለክልል ዉሃ መስኖና ኢነርጂ ልማት ቢሮ በየዓመቱ ከሚላከዉ የመጠጥ ዉሃ ግንባታ ተቋም ሪፖርት ከ 30% በላይ በመሬት ላይ ያላረፈ ፍፁም ዉሸት ሲሆን ይህ የሚደረግበት ዋነኛ አላማ በክልል ደረጃ ለማያዝና የግል ሥልጣንን ለማራዘም ሲባል ያልተገነባለትን ማህበረሰብ የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት ከመገደቡ ባሻገር በዉሃ ጥም ጉረሯችሁ ደርቆ ሰዉነታችሁ ዝሎ እንዲሁም በዉሃ ወለድ በሽታ ይለቁ ብሎ መፍረድ መሆኑን ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት መፍትሄ ያስፈልጋል

የባለሙያዎችን ሰብዓዊ መብት ማንቋሸሽና ማሸማቀቅ

ባለሙያዎች ስራ እንስራ ብለዉ ሲጠየቁ ፍፁም ኢ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ አምባ ገነናዊ በሆነ መልኩ መዝለፍና ማሸማቀቅ የዕለት ተለት ተግባር ከመሆኑ በተጨማሪ በየሻይና ቡና ቤቱ ሁሉ የስም ማጥፋትና በማጥላላት ሠራተኛዉ ከሂደት አስተባባሪዎችና ሰራተኛዉ ከሠራተኛዉ ጋር ያለዉ ግንኙነት የሻከረና ፀረ-ዲሞክራሲ እንዲሆን በማድረግ በተፈለገዉ ልክ ሥራ እንዳንሰራና ከፍተኛ ለሆነ ሠራተኛ ፍልሰት እንዲኖር አድርጎናል።

ለረጂምና አጭር ጊዜ ሥልጠና ባለሙያዎችን ተሳታፊ አለማድረግ

መንግስት የሠራተኛዉን አቅም በመገንባት የተሻለ ሥራ ለመስራትና ጥሩ ዉጤት ለማምጣት ባለሙያዉን/ሠራተኛዉን/ የረጂምና አጭር ጊዜ ሥልጠና መስጠት አንዱ የአቅድ አካል አድረጎ እየሰራ መሆኑ እየታወቀ በመስሪያ ቤታችን በየዓመቱ የሚመጣዉን የትምህር ዕድል የዚህን መምሪያ ሠራተኛ አልክም ሂዱና ክሰሱኝ እየተባልን እንዲሁም የአጭር ጊዜ ስልጠና መረጃ በተለያየ ጊዜ ሲመጣ በመደበቅ ሠራተኛዉ እንዲቆዝም፣ የተሻለ የሥራ ዉጤት እንዳያመጣ እያደረገ ይገኛል።


የጥናትና ዲዛይን እና ግንባታ ሥራዎች በተገቢዉ መልኩ አለማሰራት

የጥናትና ዲዛይን በተሸከርካሪ እና በባለሙያ እጥረት ምክንያት እንዲሁም የቅየሳ መሳሪያውን ካሊብሬት አላስደረግንም በማለት ክልል የሰጠንን እቅድ ማሳካት አለመቻላችን

ንጹህ ውሃ ፍተሃዊ በሆነ መልኩ ለህብረተሰቡ ማዳረስ የሚለውን የመንግስትን ፖሊሲ በመጣስ በተለያዩ ወረዳወች በመንግስት ወጪ ለግለሰብ ውሃ እንዲገነባ ማስደረግ

የመጠጥ ውሃ ግንባታ ወቅቱን ጠብቆ በዲዛይኑ መሰረት ባለሙያ እንዳይከታተል በማድረግና ባለሙያ የሚከታተለውን ግንባታ የመምሪያው ሀላፊና ቡድኖቹ በመከታተል ጥራቱን የጠበቀ የመጠጥ ውሃ ግንባታ በተለያየ ግዜ አለመገንባት

ሥለዚህ ያሳወቅናችሁ የድርጅትና የመንግስት አካላት ይህን ለረጂም ዓመት ያልተፈታ ቋጠሮ በማጥናት ፈታችሁልን በአገባቡ መብታችን ተጠብቆ ማለትም ሳንሰደብ/ሳንዘለፍ/ በቡድንተኝነት ሳይሆን በእኩል የሚመራ አመራር እንዲኖረን ሁኖ ለህዝብ ተገቢዉን ሙያዊ አገልግሎት እንድንሰጥ መፍትሄ እንዲሰጠን እያልን የግዴታችንን ለመወጣት ያክል እናመለክታለን።








18 12:03PM